<u>የአዝማሪና የውሃ ሙላት ተረት ፍፃሜ</u>

የሀገር አንድነት ኅልውና ደብዛው ጠፍቶ፤
የሕዝቡ አብሮ የመኖር እሴቱ ተምታትቶ፤
የነጻነት ልዕልና ማንነት ትርጉም አጥቶ፤
ዳር- ድንበሩ፤ ጠረፍ- ወሰኑ፤ ተደፍሮ፤
የአብሮ መኖር ፀጋ- ክብሩ ፤ በዘር ጥላቻ ተወጥሮ፤
በኢትዮጵያዊነት ዜግነት ኩርቶ መኖር አሳፍሮ፤
የሀገሪቱ ጉራማይሌ ቁንጅናዋ፤ በአጥፊዎቿ ተፈርፍሮ፤
በዘረኞች ዘረኝነት፤ በጎጠኞች ጎጠኝነት ትሽቀንጥሮ፤
የውገረገራል ሊገፈትር በአፍ ጢሙ ተሰባብሮ።

በአልሞት ባይ ተጋዳይነት፤ የጠራሞታል ዛሬ፤ በጥላቻ ታውሮ፤
መውደቁ ላይቀር ነገ በአንድነት ኃይሉ ተገፍትሮ ።
መካሪ አጥቶ የሚገስፀው ፤ ተው አይሆንም ብሎ የሚቆጣው፤
በፀላዒ -ሰናዮች ምክር ትጠፋለህ እያለ የሚነግረው ፤
የታሪክን ፍርድ ተገንዝቦ ፤ እቅጩን የሚያስረዳው፤
አንተ ትጠፋለህ እንጂ፤ ኢትዮጵያስ አትጠፋም ሲል የሚያረዳው ፤
አሳዳጊ የበደለው፤ ዘመድ-አዝማድ የረገመው ።

ያደቆነ ሰይጣን ገሀነመ - እሳት ሳያስገባ አይተውም እንዲሉ፤
የኸው ያደነቁራል በጎሰኝነት ቃጭሉ ፤ በዘረኝነት ደወሉ፤
በሚጠፋበት ዋዜማ ሙሾ ዋይታውን ሲያሰማ፤
ለግብዓ -ተመሬቱ የሚቆፈረው አፈር ሲለበለበው እንደ ሳማ፤
የምፀት ንግግር ተናግሮ እንዳላሰማ በደናቁርቱ ዜማ፤
ይኸው ያባንናል በጽልመት ድቅድቅ ጨለማ።

ሞት ላይቀር ፃዕረ- ሞት እንደሚሉ፤

ተጠራርጎ የጠረጋል እስከ እኩይ ግብረ - አመሉ።

" እንደ ገል ቀጥቅጨ፤፤ እንደስም አቅልጨ

ተቃዋሚዎቸን በጥይት ቆልቸ አንዱን ከሌላው አጋጭቸ ፤

በሃይማኖት ፤ በዘር ፤ በጎጥ ከፋፍየ፤

በሥልጣን ለመቆየት ፤ ሃብት ለማሸሸት ጊዜ ይመቸ ብየ፤

የሀበሾችን ፤ መሬት ለውጭ ዜጎች ሸጨ፤

ያገር ሀብት- ንበረት አውሮፓ አሜሪካ ኳታር አሸሸቼ ፤

መሹለኪያ - ማምለጫየን ፤ መሮጫየን እንዳላጣ ፤

ችግር እንዳይገጥመኝ ጣጣ- ፈንጣጣ ፤

ሸሽቴ ማይቅር ነው፤ ተዘጋጅቷል የሚያወጣ ፤

ማን ሞኝ አለ ቆሞ ሚጥብቅ የሕዝብ ቁጣ ?

ሌሎች ያልሰሩትን እኔ አልሰራሁ ?

ማንም ያልሆነውን እኔ መች ሆንኩ ?

የቱን ወንጀል ፈፀምኩ ? ማንን ዜጋ ኣስቀየምኩ ?

በታሪክና ትውልድ የሚያስወቅስ አላጠፋሁ ?

የመንግሥቱን ያህል ሰው አልፈጅሁ ?

በደም የተሞሉ ጠርሙሶች አልሰባበርኩ ?

ለገዳይ ጥይቶች ዋጋ አልጠየኩ ?

መንግሥቱ ኃይለ ማሪያምን ማን አስያዘው ?

የትኛውስ ዳኛ ፈርዶ ቀጣው ?

በሀገረ- ዝንቧብዌ ይኖር የለ ተንድላቅቆ ?

የሰረቀውን ሀብትና ንብረት አስጠብቆ ?

ይኸው ይኖር የለ ፤ በሰረቀው በሀብት ተጨማልቆ ?

በየራዲዎኑ ሲዋሽ ሕዝብ ንቆ ?

ዳግመኛ ሊያታልል ነው ድርቅና?

ወይስ የዕብደት ነው የመሃይም ድንቁርና ? "

ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ!

ለተርት ነው ወይስ ማሽሟጠጫ ?

ይኸንን ማለቱ ምድረ- ሐበሻ ?

ምን አገባው በእኔ ሽሸት መዳረሻ ?

ይልቅስ ይዘጋጅ ለሚመጣው አምባገነን፤

ለባዕዳኑ መልምል ታማኙ ጦር መኮንን ።

ለተተኪው አገልጋይ፤

ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት ባይ፤

በአዲስ ጥርሱ ንክሶ ፤ ለሚውጥ ፤

ባቋመጠ ሥልጣን ጓጉቶ ሊቀጠቅጥ ።

በስመ ዴሞክራሲ ሊያታልል ፤ ሊደልል፤

ባዕዳን ጌቶቹን ሊያገለግል ። "

የሞላ ወንዝን መሻገር የተሳነው የአዝማሪ አታልይ፤

እና

የኢትዮጵያ ፖለቲካ አካሄድ ፤ ሲያዩት ተመሳሳይ ፤

መነሻውና መድረሻው የማይታውቅ ጉዳጉድ ፤

ያልሰማው እየመጣ የሰማው ሲነጉድ ፤

መላ ቅጡ ጠፍቶበት እያባዘነ ይኖራል ፤

አዝማሪው መዘመሩን ይቀጥላል፤

ውሀውም በአሻዋው ውስጥ ሰጥሞ ይጠፋል ።

የኢትዮጵያም አምባገነኖች ወደፊት ዕድላቸው፤

እንደ አዝማሪና የውሀ ሙላት ተረት ነው ፍጻሚያቸው ።

ከነዓን

ግንቦት 2006 ዓም

////////////////////// ----------------//////////////////////